# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት አስከ ሶሰት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ሚያዚያ 6 ቀን 2004 ዓ.ም.**

**በኦህዴድ ግምገማ ላይ ባለስልጣኖቹ ተፈትሸው እንዲገቡ ተደረገ፤**
**አንድ ከስራ አስፈጻሚነት ሶስት ከማዕከላዊ ኮሚቲነት ተነሱ፤**
**25 ካድሬዎች ደግሞ ዘብጥያ ወረዱ፤**

**ተፈናቅለው አዲስአበባ ከገቡት ገበሬዎች በርከቶቹ በቁም እስር ላይ እንደሆኑ ታወቀ፤**

**በአፋር ዜጎች ከመሬታቸው እየተፈናቀሉ ነው፤**
**አንድ የ23 ዓመት ወጣት በወያኔ መከላከያ ተገደለ፤**

**ከነዳጅ ጭማሪው ጋር ተዳምሮ የዓመት በዓል ዋጋ እጅግ አስደንገጭ ሆነ፤**

ለወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ እና ለቡድኑ ስጋት ናቸው...የራሳቸውን ቡድን ይዘው ይንቀሳቀሳሉ የተባሉ የኦህዴድ ባለስልጣናትን ለመመንጠር ይረዳው ዘንድ እስከ ዛሬ ድረስ ታይቶና ተሰምቶ ባልታወቀ ሁኔታ በዝግ አዳራሽ ግምገማ እየተደረገና ምንጠራው እየተጡዋጡፈ መሆኑ ከአዳማ ናዝሬት የደረሰን ጥቆማ ገለፀ::

የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ገዥ ነው የሚባልለት እና የህወሀት ተለጣፊ የሆነው ኦህዴድ እጅግ አጣብቂኝ በሆነ መልኩ በዝግ አዳራሽ ውስጥ ጥብቅ ግምገማ እያደረገ መሆኑ ታውቆዋል::

ከሌላው ግዜ በተለየ ሁኔታ ግምገማውን ለየት የሚያደርገው ይሄ የሰሞኑ ጭቅጭቅ የኦህዴድ እና የወያኔ ባለስልጣናት ጭምር የታጨቁበት እና የታጎሩበት ከመሆኑም በላይ ከአባዱላ እስከ ሙክታር ......ከዘላለም እስከ አብዱላሂ......ከአለማየሁ ተገኑ እስከ ኩማ ደመቅሳ እንዲሁም ሌሎች የተሳተፉበት መሆኑም ታውቆዋል::

ግምገማው እየተካሄደ ያለው በአዳማ ገልማ አባገዳ አዳራሽ ተብሎ በሚጠራው ውስጥ ሲሆን ማንኛውም ባለስልጣን ሞባይል ስልክና ሽጉጥ ለጥበቃ አስረክቦ ከእግር እስከ ጥፍሩ ድረስ ተፈትሾ እንዲገባ ከመደረጉም በላይ ማንኛውም ባለስልጣን መኪናውን ይዞ እንዲመጣ ሳይፈቀድለት ለ7 ቀናት ከአዳራሹ ሳይወጡ በዚያው .....ውለው..... አምሽተው.....ለማደር እንደተገደዱም ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ለማወቅ ተችሎዋል::

ዙሪያ ጥበቃው በልዩ የኦሮሚያ ኮማንዶ ጦር ታጥሮ በግምገማ ላይ ያሉት የወያኔ ተለጣፊ የኦህዴድ ባለስልጣናት ከመጋቢት 22 ቀን 2004 ዓ.ም ጀምሮ በዚሁ አዳራሽ ውስጥ እርስ በርስ ሲላተሙና ሲፋለሙ የሰነበቱ ሲሆን እጅግ ቁጥራቸው የበዙ ባለስልጣናት ከኃላፊነታቸው የተነሱ መሆኑንም ለማወቅ ተችሎዋል::

ከቅርብ ግዜ ወዲህ በወያኔ ቡድን ውስጥ ሰፊ ልዩነት እየታየና እየጎላ በመጣበት በአሁኑ ወቅት የኦህዴድ ባለስልጣናት የመለስን ግለሰባዊ አምባገነንነት በመቃወምና ውስጥ ውስጡን ለመፈንገል አሲረዋል በሚል ልዩ ክትትል ሲደረግባቸው የቆየ ቢሆንም አሁን ግን በመለስ ቅርብ በሆኑት በእነ ሙክታር ከድር አጋላጭነት ብዙ የኦህዴድ ባለስልጣናትን ከስልጣን አባርረው ወደ ዘብጥያ ለማውረድ እየተጣደፉ መሆኑንም ከአዳማ የደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል::

ግምገማውና ምንጠራው ገና ቀጣይ ቢሆንም የኦህዴድ ካድሬዎችን በወያኔ ላይ እንዲያመጹና የመለስን ስልጣን እንዲቀናቀኑ የሚያደራጁ ዋነኛ ናቸው የተባሉትን አራት ባለስልጣናት በሙስናና በመልካም አስተዳደር ብልሹነት በአቅም ማነስ እየተሳበበ ከስልጣናቸው እንዲነሱ የተወሰነ ሲሆን እጅግ ቁጥራቸው የበዛው ባለስልጣናትም ሰሞኑን ወደ ዘብጥያ ሊወረወሩዋቸው በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ከቦታው የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል::

ወትሮም የመለስ ጣት ተቀስሮበት የነበረውና የቡድኑ ዋነኛ አንቀሳቃሽ ነው የተባለው የኦሮሚያ ምክትል ፕሬዝዳንት እና የግብርና ቢሮ ኃላፊ የነበረው ዘላለም ጀማነህ ከስልጣኑና ከኃላፊነቱ ሙሉ በሙሉ የተነሳ ከመሆኑም በተጨማሪ ከኢህአዴግ ስራ አስፈሚነት እንዲሰናበትም ተደርጎዋል::

ከዚህ ቀደም በቤተ መንግስት ውስጥ የኢህአዴግ የስራ አስፈፃሚ ስብሰባ ላይ ጉዳዩ ተነስቶ ለውይይት ቀርቦ ስምምነት ላይ ባለመደረሱና ውይይቱም በሁለት ጎራ ከፍሎዋቸው የነበረ ሲሆን በምስጢር በመለስ ዜናዊ ትዕዛዝ ከስራ አስፈጻሚነቱ እንዲነሳ ከተወሰነ ወራት የተቆጠረ መሆኑን በዜና ዘገባችን ላይ በተደጋጋሚ ማንሳታችን ይታወሳል::

ሌላው ሰሞኑን ከተሰናበቱት ባለስልጣናት መሀከል የኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የነበረው የበረከት ስምኦን ምክትል የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ሚኒስትር ደኤታ አለማየሁ እጅጉም የመባረር

እርምጃ የተወሰደበት ሲሆን  ከኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ ሙሉ በሙሉ እንዲሰናበትም መወሰኑ ታውቆዋል::

የወያኔ ቡድን በኦሮሚያ ክልል ሁለት እግሩን እንዲያቆም ትልቅ ሚና እና ድርሻ ሲወጣ የነበረው እሸቱ ደሴ የተባለው የኦህዴድ ዋነኛ ሰውም ከኦህዴድ ጽህፈት ቤት ኃላፊነት ተባርሮ ከማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነቱም እንዲሰናበት መደረጉ ታውቆዋል::

የኦሮሚያ ማዕድንና ኢነርጂ  ቢሮ ኃላፊ የነበረው ታሪኩ ነገራም በተመሳሳይ ከኦህዴድ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባልነቱና ከቢሮ ኃላፊነቱ እንዲባረር የተደረገ ሲሆን ሌሎች ለጊዜው ስማቸው ያልተገለፀው ብዙዎቹ በአሁኑ ሰዓት በቁም እስር ላይ እንዲሆኑ መደረጉ ታውቆዋል::

ከአስራ አምስት ቀናት በፊት የኦሮሚያ ከፍተኛ ሃላፊ የነበሩት ባለስልጣናት በሙስናና በብቃት ማነስ በሚል ሰበብ ከስራቸው እንዲባረሩ ተደርጎ ከስልጣናቸው የተሰናበቱ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በአቅራቢያቸው በሚገኙ የወያኔ/ኦህዴድ ጽህፈት ቤቶች ሪፖርት እንዲያደርጉ መታዘዙንም ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

የኦህዴድ አኩራፊ ቡድንተኛ ባለስልጣናትን ማረጋጊያ ተብሎ የተወሰደው ይሄው የመጀመሪያ ዙር ግምገማ ከአስራ አምስት ቀናት በፊት በተለያዩ ቦታዎች በተደረገ ምንጠራ ቁጥራቸው የበዙት እንዲነሱና እንዲንሳፈፉ የተደረገ ሲሆን እንቅስቃሴያቸው  እና ውሎዋቸው ሳይቀር በደህንነት ልዩ ክትትል እየተደረገባቸው እንደሚገኝም የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ይሄንኑ የመጀመሪያ መረጋጊያ ምንጠራ ተከትሎ ባለፈው ሳምንት የተጀመረው ዋናው የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ግምገማ ከዚህ ቀደም ዝንብ ናችሁ ብሎ መለስ እንደሰደባቸው ሁሉ አሁንም የኦነግ አጨብጫቢና አጎብዳጅ የሚል ታፔላ ጭምር እንደተሰጣቸው ከስፍራው ከተገኘ ዜና ታውቀዋል::

በቅርቡ የኦሮሚያ ክልል  ፕሬዝዳንት ሆኖ የተሾመውና የኦህዴድ ሊቀመንበር የሆነው አለማየሁ አቶምሳ በገጠመው ብርቱ የጤና መታወክ እስከ ዛሬዋ ዕለት ድረስ ወደ ስራም ሆነ ግምገማ ያልገባ መሆኑም ታውቆዋል::

የሀገሪቱ ቁልፍ ስልጣን እስከ መቼ በአንድ ግለሰብ ይያዛል? የፌዴራል መዋቅር ከሆነ በህዝብ ብዛት ፤በመሬት ቆዳ ስፋት እና በሀብት ክምችት ቀዳሚ የሆነው ክፍል በተራ ሊደርሰው ሲገባ እንደ እርስት በአንድ ቡድን ያውም በአንድ ግለሰብ ስልጣን ተይዞ የሚቀጥለው እስከ መቼ ነው በማለት በተደጋጋሚ ግዜ ሲያነሱ የነበሩት እነ ዘላለም ጀማነህ በነመለስ ጥቁር መዝገብ ውስጥ በመግባታቸው ጊዜ ተጠብቆ እርምጃ እንደተወሰደባቸው የጠቆመው ከአዳማ የደረሰን ዘገባ ጥያቄው የኦህዴዶች ብቻ ሳይሆን የብአዴኖችም ጭምር በመሆኑ ሁለት እና ሶስት ሰዎችን ከስልጣን አባርሮና አስሮ ይዳፈናል ማለት ዘበት ነው ሲሉም ብዙዎቹ የኦህዴድ ባለስልጣናት እየተናገሩ ይገኛሉ::

በተያያዘ ዜና ከአዲስ አበባ ከተማ አጠገብ በምትገኘዋ በቡራዩ ከተማ ካድሬዎች በዝግ አዳራሽ ውስጥ ከፍተኛ ግምገማ እያደረጉ መሆኑ ታውቆዋል፡፡

ሰሞኑን በተጀመረው ጥብቅ ግምገማ ሙስና እና የብቃት ማነስ እየተባለ ብዙ ሰበብ የሚሰጥው ቢሆንም ከዋናዎቹ የኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት ጋር ጠዋት ማታ እንደሚገናኙ በመታመኑ የቡራዩ ከተማ አስተዳደር ዋና ዋና የተባሉትን ከስልጣናቸው አንስተው ለእስር እንደዳረጉዋቸው ታውቆዋል፡፡

ከእነ ዘላለም ጀማነህ ጋር ትስስር አላቸው ተብለው ከተጠረጠሩት መሀከል እንደሚገኙበት የታወቀ ቢሆንም ምክንያቱን ቀይረው ከመሬት ጋር ተያይዞ የቡራዩ ከንቲባን ጨምሮ አስተዳደር ውስጥ ሲሰሩ የነበሩት 25 ካድሬዎች ሰሞኑን አስኮ በሚገኘው ሳንሱሲ  እስር ቤት እንዲገቡ መደረጉ ታውቆዋል፡፡

መሬት እንደ ሸንኩርት ሲቸበቸቡ እየተስተዋለ ህዝቡ አቤት ሲል በነበረበት ወቅት እነ መለስ ዜናዊ ፖለቲካውን እስከ ደገፈ እና ትዕዛዝ እስከተቀበለ የፈለገውን ያድርግ ብለው በር ከፍተው ሰጥተው ሲያስቦጭቁ እንዳልነበር ዛሬ ድንገት ክፍፍሉ እየሰፋና እያደገ በመምጣቱ ስጋት የገባቸው እነ መለስ ዜናዊ በሙስና እና በብቃት ማነስ በሚል ምክንያት ወደ ዘብጥያ እንዲወርዱ ማድረጋቸውም ታውቆዋል፡፡

በተመሳሳይ እንደ ኦሮሚያና ሌሎች ክልሎች ሁሉ በፖለቲካ ተወጥረው የሚገኙት የወያኔ ተለጣፊ የሱማሌ ክልል ባለስልጣናትም ሰሞኑን በዝግ ግምገማ ላይ እንደሰነበቱና ከፍተኛ ባለስጣናቱም እንደተባረሩ ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ ገለጸ፡፡

ከመጋቢት 24 ቀን ጀምሮ እስከ ሚያዚያ 4 ቀን 2004 ዓ.ም ድረስ በተደረገ አዲስ ዝግ  ግምገማ ሶስት ከፍተኛ የክልሉ  ባለስልጣናት ከኃላፊነታቸው ሲነሱ ቁጥራቸው የበዛ የዞን ባለስልጣናትም በተመሳሳይ መባረራቸው ታውቆዋል፡፡

ከአዲስ አበባ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር ቢሮ በተላኩ ሁለት የወያኔ ባለስልጣናት መሪነት በተደረገው ዝግ ግምገማ ከኦጋዴን ብሔራዊ ነጻ አውጭ ግንባር ጋር ግንኙነት አላችሁ በሚል ስድብና ማስፈራሪያ ሲሰነዘርባቸው የሰነበቱ ቢሆንም የከፋና እጃቸው የቦካ የተባሉትን ግን ከስልጣናቸው እንዳባረሩዋቸው ከጅጅጋ የደረሰን ዘገባ ገልጾዋል፡፡

ከስደስት ወር በፊት በአዲሱ አደረጃጀት የተሾሙት ሶስቱ የሱማሌ ክልል ምክትል ርዕሰ መስተዳድሮች የፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ሃላፊ አህመድ ዴቅ ፤የከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊ አደን ፋራህ፤የእንስሳት እና እርሻ ምርምር ተቁዋም ዳይሬክተር ዶክተር ሱልጣን ወሌ መሆናቸው ሲታወቅ ከህዝቡ ጋር ጥሩ ግነኙነት ስላላቸው በፍርሀት እንዳነሱዋቸው ይሄው የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል፡፡

በኦህዴዶች ላይ የተጀመረው ምንጠራ ወደ ሱማሌ ክልል ባለስልጣናት የተሸጋገረ ከመሆኑም ባሻገር ቀጣይም ወደ ጋምቤላ እና የተቀሩት ክልል ውስጥ እንደሚዘልቅ ይጠበቃል፡፡

ወያኔ በአሁኑ ሰዓት እጅግ በፍርሀት ውስጥ ተወጥሮ ያለበት ወቅት ሲሆን የፍርሀቱ ምንጭ ዋነኛው በውስጣቸው የተፈጠረው ክፍፍል እየሰፋና እያደገ በመምጣቱ ለመለስ ዜናዊ የስልጣን ወንበር አደጋ ሊፈጥር ይችላል ከሚል የመነጨ ሳይሆን እንዳልቀረም እየተነገረ ይገኛል።

በሌላ ዜና በደቡብ ክልል ፕሬዚዳንት በአቶ ሽፈራው ሽጉጤ ፊርማ በተላለፈ ደብዳቤ ከደቡብ ክልል ከቤንች ማጂ ዞን ወደ 80 ሺ የሚጠጉ አማራ ገበሬዎች እንዲባረሩ ትእዛዝ ተላልፎ የመጀመሪያው ዙር ከጉራ ፈርዳ ቀበሌ ወደ 8ሺ የሚደርሱ አባወራ ገበሬዎች ከእርሻቸው፤ከቤትንብረታቸው መፈናቀል ከጀመሩ 2 ሳምንት አልፏል። ከየቤታቸው በኃይል እንዲወጡ በተደረገ ጊዜ የቆሰሉና ሕይወታቸው ያለፈ ዜጎች እንደነበሩ ገበሬዎቹ ይናገራሉ።ከአከባቢው በሚወጡበት ጊዜ ቤታቸውን ከብቶቻቸውን ለመሸጥ ገበያ ያወጡ የአከባቢው ሕዝብ እንዳይገዛቸው ጥብቅ መመሪያ በመተላለፉ ገዥ አጥተው ተመልሰዋል። የደቡብ ክልል ፕሬዚዳንት ከአሁን ቀደም ከአቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ጋር የሲዳማ ሕዝብን የጨፈጨፈ አረመኔ መሆኑ የታወቀ ነው። ይህ ሰው ከአከባቢው ምንም የተፈናቀለ ሰው እንደሌለ ሽምጥጥ አድርጎ ክዷል።ተፈናቃዮቹ አዲስ አበባ ከደረሱ በኋላ በቤተክርስቲያን መጠለያ ለማግኘት ያደረጉት ሙከራ በአረመኔው በጨከኙ ጳጳስ ትእዛዝ ከየቤተክርስቲያኑ እንዲባረሩ ተደርጓል።የተወሰኑ ገበሬዎች በመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት ቢሮ ድርጅቱ ባደረገላቸው ትብብር ለተወሰኑ ቀናት አርፈዋል።በመጨረሻም በአማራ ሕዝብ ስም የሚነግደው ብአዴን የሚባለው የወያኔ ተላላኪ ድርጅት በኃይልና በማስፈራራት ከመኢአድ ቢሮ አውጥቶ ገሚሱን ወደ ደብረብርሃን የተቀሩትን ደግሞ አዲስ አበባ ጋዜጠኞችና የሰብአዊ ድርጅቶች ሊያዩዋቸው በማይችሉበት ሰዋራ ቦታዎች በቁም እስር እያስቃዩዋቸው እንደሆነ መረዳት ተችሏል። ከመካላቸው የአድማ መሪ በሚል በሰደፍና በእርግጫ እያዳፉ ጭርሱኑ ደብዛቸው የጠፋ እንዳሉም ታውቋል። ከእነዚህ ገበሬዎች መሃል አዲስ አበባ የከ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 14 ቁስ ሰፈር ተብሎ በሚጠራው አከባቢ የወጣቶች ማእከል ጊቢ ውስጥ ከ300 እስከ 400 የሚገመቱ ገበሬዎች በቁም እስር ላይ እንዳሉ ታውቋል። ይህ ማእከል ዙሪያውን በወያኔ ፌዴራል ፖሊስ የተከበበ ሲሆን ከተፈቀደለት በስተቀር ወደ ውስጥ መግባት አይቻልም። ከገበሬዎች መሀል አዲስ አበባ ዘመድ ያላቸው ለመውጣት ቢጠይቁ የተሰጣቸው መልስ ከዚያች ግቢ መነቃነቅ እንደማይችሉ ነው። እንዲተኙ የተደረገው ባዶ ሲሚንቶ ወለል ላይ በመሆኑ ለሳንባና ለሌሎች በሽታዎች በቀላሉ እንደሚጋለጡ የሕክምና ባለሙያዎች ይናገራሉ።የአከባቢው ኑዋሪዎችና ሌሎች በጎ አድራጊ ወገኖች በተደጋጋሚ ምግብ ለማብላት ያደረጉት ጥረት ከገበሬዎቹ ጋር መገናኘት እንደማይቻሉ ስለተገለፀላቸው ሳይቻል ቀርቷል። የብአዴን ከድሬዎች በሕጋዊ መንገድ ተረክበው ያርሱት ለነበረው መሬት የከፈሉባቸውን ደረሰኞች በማስፈራራት ወስደውባቸዋል። ይህን ዘግናኝ ጉዳይ በቅርበት የተከታተሉ ታዛቢዎች ወያኔ ፀረ ሕዝብ ሆኖ እሱ የወለደው ብአዴንም ፀረ ኢትጵያ ፀረ አማራ እንጅ ሌላ ሊሆን አይቸልም ይላሉ።ለእነዚህ ጉስቁል ገበሬዎች እንደ ቀይ መስቀል፤ የሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች ጋዜጠኞች የፖለቲን ድርጅቶች ሊጮሁላቸው ይገባል። ወያኔ አንዱ ላይ የሚፈፀመው በሁሉም ላይ ነውና እነዚህ ጉስቁል ገበሬዎች መገፋት መረገጥ የሁላችን መገፋተ ነውና፤ ለእነሱ ስንታገል ለራሳችነም ነውና የሚሉ አስተያየቶች ይሰማሉ።

በሌላ ዜና ህዝብ የእለት ጉርስ መቅመስ ተቸግሮ ባለበት በአሁኑ ወቅት ሰሞኑን ከደቡብ ክልል የአማራ ብሔር ተወላጆችን የማፈናቀል ስራ ከተሰራ በሁዋላ ወደ አፋር ክልል መዛመቱ ታወቀ::

የአፋር ብሔር ተወላጆች እትብታቸው ከተቀበረበት ቀዬ በግዴታ ያለ ምንም ካሣ ክፍያ ይዞታቸውን ለቅቀው እንዲወጡ በመገደዳቸው በተፈጠረ ግጭት ቁጥራቸው የበዙ ዜጎች ድብደባና እስራት እንደደረሰባቸው ለማወቅ ተችሎዋል::

ባለፈው ሳምንት ከአያቶቻቸው እና ቅድመ አያቶቻቸው ሲተላለፍላቸው የነበረውን ይዞታ በመልሶ ማልማት ሰበብ ያለ ምንም ግምት በነጻ አስረክበው ስፍራውን ለቅቀው እንዲወጡ በመባላቸው በተፈጠረ ግጭት ህዝብ በዱላ እየተቀጠቀጠና በጥይት ሲቆላ እንደሰነበተ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

በአፋር ክልል የአዋሽ ወንዝ ተፋሰስ ላይ ያሉ የዱብቲና የአሳይታ ነዋሪዎች ያለ ቅድመ ማስጠንቀቂያ ለሸንኮራ ተክል ልማት ስለሚፈለግ አካባቢውን ለቅቃችሁ ውጡ በመባላቸው ብዙዎቹ ያለ መጠለያ በተለያዩ ከተሞች ለጎዳና ህይወት የተዳረጉ ሲሆን ቀሪዎቹ እትብታችን የተቀበረበት ቀዬ በመሆኑ አንለቅም ሲሉ ከወያኔ መከላከያ ሰራዊት ጋር ግጭት መፍጠራቸው ታውቆዋል::

ይህንኑ ግጭት ተከትሎ በክልሉ በተለይ በአሳይታና በዱብቲ ከተማ እና አቅራቢያ የሚገኙትን የአፋር ተወላጆች ሴት ወንድ...ህጻን አዋቂ.....ሽማግሌ አሮጊት ሳይሉ በዱላ ከመደብደባቸው በተጨማሪ አራሶችን ጭምር እያፈሱ ግድግዳ በሌለው እስር ቤት ውስጥ እያጎሩዋቸው ብዙዎቹ በብርድ በሽታ መጠቃታቸው ታውቆዋል::

አስታራቂ፤ ወቃሽና መካሪ የነበሩት በአፋር ብሔር ተወላጆች ዘንድ ከፍተኛ ክብር የሚሰጣቸው የአፋር አባቶችን ጭምር በዱላ እና በሰደፍ የወያኔ መከላከያ ሰራዊት ሲቀጠቅጡዋቸው እንደነበረ የአይን እማኞች ከስፍራው ያደረሱን ዘገባ ገልጦ በአሁኑ ሰዓት የመብት ጥያቄ የሚያነሳውን የአፋር ብሔር ተወላጅ የሻዕቢያ ተላላኪ በሚል ለከፋ ስቃይ እና እንግልት እየዳረጉዋቸው እንደሚገኝ ዘገባው ጨምሮ ገልጾዋል::

ለስኩዋር ልማት በሚል ከአርሶ አደሮቹ ላይ ያለ አንዳች ካሳ ክፍያ በነጠቁት መሬት ሳቢያ በተከሰተው ፀብ የተነሳ ብዙዎቹ በጥይት እና በዱላ የተመቱ ከመሆኑም በላይ አንድ የ23 ዓመት ወጣት በደረሰበት ከፍተኛ ድብደባ ህይወቱ ሊያልፍ እንደቻለና በአሁኑ ሰዓት የወያኔ መከላከያ ሰራዊት ቤት ለቤት አሰሳ እያደረገ ዜጎችን እየደበደበ ለእስር እየዳረጋቸው መሆኑም ተጠቁሞዋል::

በመጨረሻም በየጊዜው በሚፈጠረው የኑሮ ውድነት የተነሳ ህዝብ በከፍተኛ ችግር ውስጥ ተዘፍቆ ባለበት በአሁኑ ወቅት የወያኔ ቡድን ድንገት የነዳጅ ዋጋ ጭማሪ በማደረጉ ወደ ከፋ የኑሮ ቀውስ እየተሸጋገረ መምጣቱን ተዘዋውሮ ከተመለከተው ዘጋቢያችን የደረሰን ጥቆማ ገለፀ::

ሰሞኑን በተደረገው የነዳጅ ጭማሪ ብዙሀኑ ህዝብ የሚጠቀምበት ናፍጣ ላይ ሲሆን ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቀድሞ ከነበረው የኑሮ ውድነት ሰሞኑን ወደ ከፋ ሁኔታ መሸጋገሩን ከላከው ዘገባ መረዳት ተችሎዋል::

ቀድሞም የኑሮ ውድነቱ እየባሰና እየከፋ በመጣበት በአሁኑ ወቅት ዓመት በዓሉ እና የነዳጅ ዋጋ ጭማሪውን ተከትሎ የዋጋ ጭማሪው አስደንጋጭ የሚባል ደረጃ መድረሱ ታውቆዋል፡፡

የነዳጅ ዋጋ መጨመሩን ተከትሎ የትራንስፖርት ታሪፍም ጭማሪ በመደረጉ የእህል እና የጥራጥሬ እንዲሁም የሌሎች ሸቀጦችም ዋጋ ሊንር እንደቻለ ከህዝቡ እሮሮ የተረዳው ተዘዋዋሪ ዘጋቢያችን ወትሮ አንድ ኩንታል 1300 ብር ሲሸጥ የነበረው ጤፍ ዛሬ 1800 ብር መድረሱን ለማረጋገጥ ችሎዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት አንድ ዶሮ ከ200 እስከ 250ብር፤ አንድ እንቁላል ከ2 ብር ከ50 በላይ፤መለስተኛ በግ ከ5 ሺህ ብር በላይ በቡድን ቅርጫ ለማረድ እንኩዋን እንዳይቻል በሬ ከ20ሺህ ብር በላይ ዋጋ የናረበት ወቅት መሆኑን አረጋግጦዋል፡፡

የአንድ ኪሎ ሽንኩርት ዋጋ 4 ብር የነበረው ወደ 12 ብር ያደገ ሲሆን ፤የአንድ ኪሎ ቅቤ ዋጋ 220 ብር እንደሆነም ተዘዋውሮ ከተመለከተው ዘጋቢያችን ካደረሰን ጥቆማ ለማረጋገጥ ተችሎዋል፡፡